# መካር የሌለው ንጉስ ያለአንድ ዐመት አይነግስ!

ከጎችዬ እንግዳ

የህይወት ገጠመኞች ብዙ ያስተመራሉ። አባቶቻችን በተረት፤ በምሳሌና በተውፌት መልክ ያስተላለፉልን ሁሉ ሕያው ሆነ፤ በእኛም የዕለት በዕለት መስተጋብራዊ ህይወታችን ይታያሉ። ይህንን ያነሳሁት ስለ አባቶቻችን ትርክት ለመሰንዘር ሳይሆን በተለይም እኛ ኢትዮጵያውያን ካለፉት 30 ዓመታት ጀምሮ እንደ ሀገርና እንደ ዜጋ እየገጠመን ያለው ችግር፤ ሰላም ማጣት፤ በእንቶፈንቶው እርስ በእርስ መሻኮትና እየዳከርንበት ያለውን የድህነት አዙሪት ቀለበት መሰበር አቅቶን እየዋተትንበት የምንገኝበትን ጎዳና ለመግለጽ ነው።

ትህነግ-ኢህአዴግ እና ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑት ግብረአበሮች፤ የኦሮሞ ድርጅቶችና ልሂቃን የስልጣን ማማውን በጠመንጃ ሃይል ከነጠቁበት  ጊዜ ጀመሮ እየተመሩባቸው ያሉት ጠባብ ብሄረተኛነትንና ዘረኝነትን የተላበሰ ተግባራቸው በህዝብ መካከል ሰላም፤ ፍቅርና አብሮነትን እየደበዘዘ ዕንዲመጣ አድርጓል። የእኒህ የሰይጣን መልዕክተኞች ደናቁርታዊ መመሪያ ያስከተላቸው ጀሌዎችም፤ትላነት ህዝባችን በአብሮነት የፈጸማቸውን ገደሎች፤ እንዳልነበሩ ከመተረኩም በላይ፤ ወልዶ፤ ተዋልዶ፤ ተቀላቅሎና እንደ ሸረሪት ድር የተወሳሰበውን አንድነት በጎሰኛነት ፖለቲካ ለመተካት በፈጠሩት የእርስ በርስ መጠላለፊያ ገመድ አስሮ በመተብተብ የአንድነቱን ምሶሶ እያናጋ የገኛል።ይህንን የጥፋት ተልዕኮውን ለመተግበር የሄድበት መንገድ ሲታይ፤

- ከፋፋይ ህገመንግስት  አጽድቆ ተግባራዊ ማድረግ፤
- ክልል የሚል መዋቅራዊ ይዘት በመፍጠር ግለኝነትን ማዳበር
- በጎሳና ጎሳ መካከል የድንበር ግጭት እንዲፈጠር ማድረግ፤
- ከእኛ ይልቅ የእኔነት ሥነ ልቦናዊ አምልኮ እንዲዳብር ማደረግ፤
- ኢትዮጵያዊነትን የሚያራምዱ ሀይሎችን በረቀቀ ዘዴ ማጥፋት፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ የአብሮነትና የአንድነት ታሪክ እንዳልነበር በማስመሰል መስብክ፤
- የፕሮፖጋንዳና የቅስቀሳ ተግባሮቻቸውን በረቀቀ መንገድ በማካሄድ የህዝብን ተዓማኒነት ማግኘት፤ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።

የዚህ እቅድ አፈጻጸም ላለፉት ሦስት አስርታት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሲተገበር ከረሚል። ትህነግ ኢህአዴግ ለሀያ ሰባት ዓመት ኢትዮዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የቆፈረው ጉድጓድና የሸረበው ሴራ እጅግ ውስብስብ ቢሆንም ከታሪክና ከሕዝብ የሚሰወር ምንም ዓይነት ረቂቅ ምስጢር ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ኢትዮጵያውያን የትህነግን ምስጢር ባውቁ፤ ባውጡና ባጋለጡ  ቁጥር አሰቃቂ ግፍና በደል እየተፈጸመባቸው ሀገራችንን ለመታደግ በቅተዋል።

ትህነግ ወያኔ ህዝባችንን  እየገደለ አስተዛዛኝ ሆኖ የመቅረብ ቲያተሩ ቀስ በቀስ እየታወቀ ሲመጣና ህዝባዊ ዐመጹም ከዳር እስከዳር ሲቀጣጠል ከአካሉ በወጣው፤ ባሳደገውና በገራው ሀይል ተተክቷል።

ተተኪ ሀይሎች ወያኔን ለመተካት ከውስጥ ሆነው ወያኔ ለረዥም ጊዜ ሲያከናውነው ከነበረበት መንገድ ወጣ ብለው ያሴሩትና ያመጹት፤ ለኢትዮጵያ ህዝብ ተቆርቁረው ሳይሆን፤ ይህ እያስገመገመ  የመጣው ህዝባዊ ማዕበል እነርሱንም ጠራርጎ እንዳይወስዳቸው በመስጋት ነው። የሞተ አህያ ጅብ አይፈራም እንዲሉ በማዕበሉ ተጠራርጎ ከመጥፋት፤ማመጽ ምንም አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን መርጠው በመቀበል ነው። በሌላም በኩል ቀድሞውንም በኢህአዴግ ስር ያሰባሰባቸው ኢትዮጵያዊነት ሳይሆን ዘረኛነት ፤በመሆኑ በአጋጣሚው የጎሰኛ ድርጅታቸው ሻምፒዮና ሆኖ ብቅ ለማለት ነው። ይህም እንደተስተዋለው  የፖለቲካ ምህዋራቸውን በጎሳቸው ላይ ለመመስረት ማለማቸው እጅግ ውስብሰብ ለሆነ፤ታሪክ ይቅር ለማይለው ጥፋት ዳርጉቸዋል።

የዚህ ቡድን ቁንጮ የሆነው የቀደሞው ኦህዴድ የአሁኑ ኦዴግ ሊቀመንበር ዶር ኮረኔል አብይ አህመድ የስልጣን ርካቡን ለመቆናጠጥ ባደረገው ሙከራ ኢትዮጵያዊ መስሎ መቅረቡ የአብዛኛውን ህዝብ ቀልብ ስቧል። በተለምዶ ቲም ለማ የሚባለው ለውጥ አርማጅ ነኝ ባዩ ቡድን ለምን ፍጹም ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለመቅረብ ሞከር የሚል ጥያቄ በብዙዎቻችን ዘንድ ይነሳል፤ መልሱ ግን እጅግ በጣም ቀላል ነው። ለማም ሆነ ዐብይ በኢህአዴግ-ኦህዴድ አቅራቢነት በኢህአዴግ-ትህነግ አጽዳቂነት ተመልምለው ሲኮለኮሉ ከአመታት ክትትል በኋላ ብቃትና ታማኝነታቸው በመረጋገጡ በደህንነት መስሪያ ቤት ውስጥ ተመደበው እንዲሰሩ ተደርጓል። በዚህ መሰሪያ ቤት በሃገር ውስጥ ደረጃ የሚከናወነው ዋናው ተግባርሕዝብ ምን አለ የሚለውን የሕዝብ ፍላጎትና አመለካከትን መረዳትና ማውቅ ሲሆን፤ግለሰቦቹ በተሰማሩበት የሥራ መስክ ያካበቱት፤ቁም ነገር፤የኢትዮጵያ ህዝብ በኢትዮጵያዊነቱ፤በሀገሩ ልዕልና፤ በዳር ድንበሩና በኢትዮጵያ ታሪክ ኩራት ላይ ያለውን ቀናዒ አመለካከት በጥልቅ እንዲገነዘቡ እንደረዳቸው ይገመታል።

በመሆኑም በህዝባዊ ማዕበሉ ውስጥ በመግባት ተጸእኖ ፈጣሪ ሆነው የሀይለማሪያምን መንግስት የመልቀቂያ ጥያቄ እንዲያቀረበ ግፊት አድርገዋል።በኢአሃዴግ ውስጥ በተደረገው ሽኩቻ በደመቀ መኮንን አማካይነት ወደ ስልጣን ማማው ሊንጠላጠሉም በቅተዋል። ሥልጣን ላይ ከወጡ በኋላም ቀደም ሲል በድህንነት ስራተኛነታቸው የሰበሰቡትን መረጃ ወደ ተግባር በመለወጥ   ኢትዮጵያዊነትን አቆላምጠውና አሞካሽተው በቅጽል የታጀቡ ንግግሮችን ማደረጋቸው በብዙዎቹ ዘንድ የዓምላክ መልዕክትኛ አስመስሎአቸው ነበር። ከስልጣን ርክክብ በኋላም የውሰዷቸው የዕርማት ንቅናቄዎችና እንዚህኑ ውሳኔዎች ለማጠናከር የውሰዷቸው እርምጃዎች ተቀባይነታቸውን ይበልጥ ጭመሮታል።

እነዚህ ሀይሎች የወጡት በኋለኛው ዘመን በኢህአዴግ ውስጥ በተከናወነ የሁለት መስመር የፖለቲካ ትግል አሸንፈው እንጂ የተለየ የፖለቲካ ራዕይና ፕሮግራም ኖሯቸው አይደለም። ለውጥ፡የለም፡ኢሃአዴግ ከጅመሩና በኋላም በሂደቱ እጅግ ብዙ ግዙፍ ስህተትና ጥፋት ሰረቷል። ዛሬ ልውጥ እየተባለ የሚሞካሸው እነዚህ ስህተቶች እንዳይደገሙ እየተከናውነ ያለ የዕርምት እቅስቃሴ ነው።
የኢህአዴግ ግንባር በመሰረቱ ከተመሰረተበት ዓላማ ፈቀቅ አላለም። እየተካሄድድ ያለው የዕርምት እንቅስቃሴ ኢህአዴግ በአፈጻጸም ደረጃ የተከሰቱ ስህተቶችን በማረም ላይ ያተኮር ነው። ትህነግ ወያኔ ለፈጸመው ግርፊያ፤ግድያ፤ኮዳ ማንጠልጠል፤ከሁሉም በላይ አገርን በማስቁረሰ፤ታሪክን በመደምሰስ፤ የአገርን ህልውናን በእቅድ የማጥፋት ክህደት ወንጀል፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የትላንት የዛሬና የዘውትር ጥያቄ ቢሆንም መፈትሄ ያለማግኘቱ አሳሳቢ ነው።

ዶር አብይ ሰላምና መረጋጋትን ለማምጣት በሃገርም ሆነ በውጭ ሃገር ያደረጉት እንቅስቃሴ ስልታዊ በሆነ መንገድ ተቃዋሚውን ወደ ተፎካካሪነት ለውጦ ወደሃገር እንዲገባ ረደቷል። የሚገርመው ጉዳይ ተቃዋሚ ነኝ የሚለው ክፍል  በቃላት ስንጠቃና በፊደላት ልዩነት የተሻኮትክና እርስ በእርሱ  የተገዳደለክ ትውልድ ነህ መባሉን ትንሽም ቢሆን ሳይንገራገር መቀበሉ የሚገርም ክስተት ነው። ሀቁ ግን ያ ትውልድ በየትም የፖለቲካ ድርጀት ወግኖ ቢገኝም፤ ምኞቱና እምነቱ ከጉልበት ልፋት እስከ ሕይወት መስዋእትነትም የከፈለው ለኢትዮጵያ ትልቅነት ብልጽግና ለህዝቧ ደህንነትና ክብር እንድ ነበር በውስጡ ያለፍነው እናውቃለን።ለዛሬውም ትግል መሰረት የዚያ ትውልድ የትላንቱ ተጋድሎና መስዋእትነት መሆኑን በመዘንጋት በአፈ ጮሌነትና ነገር ያሳመሩ መስሎአቸው የተናገሩት ጠቅላይ ሚኒስተር ሊያፈሩበት ይገባል። ያንን ትውልድ ይቅርታ መጠየቅም ብልህነትና አዋቂነት እንድሆነ መገንዘብ ይገባል።

ዶር ዐብይ የኢትዮጵያ ጠ/ሚ ከሆኑ በኋላም የፖለቲካ መሰረታቸው የወጡበት ጎሳ የሆነው የኦሮሞ እንቅስቃሴ ስረዐት አልበኛነት፤ ለህግ ተገዢ ያለመሆን፤ ተተናኳሽነት፤በጠራራ ጸሀይ ግድያመፈጸም፤ባንክ ዝርፊያ፤ኢትዮጵያዊ ነን በሚል ለርዥም ዘመን ተጋበተው የሚኖሩ ዜጎችን በመፈርጅ ማባረር፤ባጠቃላይ የመንጋ ፖለቲካ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ያልታይ የዕምነት ስፍራዎችን ማቃጠል ወዘተ  ተፈጽሟል።

በመንግስት አመራር ላይ ተቀምጠው ይህንን በታሪካችን የመጀመሪያው የሆነ አጸያፊ ተግባር በፈጸሙና አሁንም እየፈጽሙ ባሉ የመንጋ ፖለቲከኛ መሪዎች ላይ ምንም ከጥፋታቸውና ከበታኝ አንደበታቸው እንዲቆጠቡ ለማደረግ የወሰዱት ርምጃየለም። እነዚህንም ዕኩይ

ድርጊቶችን ቢያንስ አንድም ጊዜ ያለማውገዛቸው ከድርጊቱ ተካፍይ እንድሆኑ ከማስገመቱም አልፎ መንግስታቸው መካር አልባ አመራር እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም።

እነዚህ ሁሉ በታች ተገባሮች እንዳሉ ሆነው፣ ታጣቂ ሀይሎች በማን አለብኝነት በተለይም በምዕራቡ የሃገራችን ክፍሎች እይተንቃሳቀሱ የመንግስት ባለስልጣኖችን እይገደሉ፣ ዘረፋን እያከናወኑ፣ ባለበት ወቅት በልዩ ልዩ ማህበረሰቦችና ጎሳዎች መካከል የተደበላለቀ ጥያቄና አለመግባባት እያለ፣ወዘተ ወደ ምርጫ ለማከናውን የሚደረገው እንቅስቃሴ በድቡሽት ላይ የተሰራ ቤት ለመፍጠር ካልሆነ በሰተቀር ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚታደግ አይሆንም።

የችግሮቻችን ሁሉ መንሰዔየሚቀረፈውና ወደዕድገት ጉዞ ማድረግ የምንችለው፣ወያኔ ኢህአዴግ በህዝባችን ላይ የጫነው ህግ መንግሥት ሲሆን፣ ይህ ህግ መንግስት ሙሉ በሙሉ ታገዶ፣ ኢሃዴግን ጨምሮ ሃላፊነት አለብን የሚል ሁሉ የሚሳተፈበት የሽግግር መንግስት በማቋቋም የሚከናውን ስር ነቀል እርምጃ መውሰድ ሲቻል ነው።

በየትኛውም የዐለማችን የፖለቲካ እንቅስቃሴ ግለሰብ ከፈተኛ ሚና ሊኖረው ይችላል። ነገር ግን አሽጋጋሪ ሊሆን በፈሉም አይችልም። በዐለማችን ያልተፈጸመ ድርጊት በእኛ ላይ ያውም ውሰብሰብ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እየተካሄድ ባለበት አገር ሊፈጸም አይችልም።

ዶር አብይ አሁን በ11ኛው ሰዓት ላይ ቢገኙም እንደሚናገሩት ሁሉ ፍጹም ኢትዮጵያዊነታች በተገባር ለማሳየት ህገ መንግስቱን፣ ክልላዊ አደረጃጀቱን፣ በዘር መደራጀትን ማገድ የኖርባቸዋል። ከዚህም በላይ የመንጋ ፖለቲካ አካሄዶችንና አጉራ ዘለል የኦሮሞ ብሄረተኞች ላይ የማያዳግም ውሳኔ በመስጠት የኢትዮጵያውያንን አቋም ለማጠናከር ከቻሉ እንድ አጀማመራቸው የኢትዮጵያን ህዝብ ከጎናቸው ማሰለፍ ይችላሉ። ይህ ሳይሆን ቀርቶ የሃገር ህልውና አሁን ባለበት አስጊ ሁኔታ እንዲቀጥል ከተደረገ መካር የሌለው ንጉስ ያለ አንድ ዓመት አይነግስ እንዲሉ መተረቻ ይሆናሉ።

## ህግ መንግስቱና የክልል አደረጃጀት ፀረ ኢትዮጵያ ነው!!!

## ከወያኔያዊ አመለካከት ወጥተን ዘላለማዊት ኢትዮጵያን እንገንባ!!!!